# <u>መልካም ዜና</u>

## <u>በኒውዮርክ፣ኒውጀርሲ፣ኬኔክቲከት እና ቦስተን ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ትውልድ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ</u>

የኢትዮጵያ ህዝብ፣ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚመራው መንግስት ለተከታታይ ሁለት አሠርት ዓመታት ባደረጉት ያላሰለሰ የፀረ-ድህነት ትግል ሰምሮ አገራችን ኢትዮጵያ ለተከታታይ ዘጠኝ ዓመታት ባለሁለት አሃዝ እድገት በማስመዝገብ በነዳጅ ላይ ያልተመሠረተ ኢኮኖሚ ካላቸው አገራት በኢኮኖሚ እድገት ቀዳሚውን ቦታ ይዛለች።

ይህም አንገታችን አስደፍቶን የነበረውን ድህነት በመቅረፍ አንገታችንን ቀና አድርገን እንዲንሄደና በኢትዮጵያዊነታችን እንድንኩራ እድል ፈጥሮልናል። በአሁኑ ወቅት አገራችን ኢትዮጵያ የራስዋን ሰላም ከማረጋጋጥ አልፋ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም ለማስፈን የቻለች አገር ለመሆን በቅታለች፣ስሟ በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች በበጎ አስተዋፅኦ የሚጠራ ሆኗል።

አገራችን ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰብ እስር ቤት መሆንዋ አክትሞ የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በመከባበር እና በመፈቃቀድ በነጻ ፍላጎታቸው የመሰረትዋት አገር ሆናለች። ህዝቦቿም ማንም ሊነቀንቀው የማይችል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ፈጥረዋል።

በቅርቡ በአገራችን በተፈጠረው ወቅታዊ ሁኔታ የሥልጣን ሽግግር ማድረግ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እንደ ወትሮው ብስለቱን፣አርቆ አሳቢነቱንና ሊተማመኑበት የሚገባ ድርጅት መሆኑ ለኢትዮጵያ ህዝብና እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በተግባር አረጋግጧል።

ስለሆነም እኛ በኒውዮርክ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በአገራችን ውስጥ ምልዓተ-ህዝቡን በማንቀሳቀስ በአገራችን ልማት፣ሰላም እና ዲሞክራሲ እንዲሰፈን ሌት ተቀን የሚተጋውን ድርጅትና መንግስት በመደገፍ በአገራችን ልማትና እድገት ሁለንተናዊ አስተዋፅኦ ለማበርከት እንድንችል ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ በማቋቋም የኢ.ህ.አ.ዴግ ደጋፊዎች ፎረም ለመመስረት በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን።

***ስለሆነም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚመራውን ልማታዊ መንግስት በመደገፍ ድርሻችሁን ለማበረከት የምትፈልጉ ሁሉ በተቻለ ፍጥነት ሙሉ ስማችሁን፣የፖስታ አድራሻና ስልክ ቁጥር በ eprdfs@yahoo.com በመላክ ወይም በስልክ ቁጥር 646-322-3834 በመደወል እ.አ.አ እስከ ኖቬምበር 08/2012 ድረስ እንድትመዘገቡ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል።***

ከሰላምታ ጋር

የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊዎች ፎረም አደራጅ ጊዜያዊ ኮሚቴ

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!!

10/08/2012